# <u>የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ታሪክ</u>



ኢትዮጵያ ጥንታዊ ከሚባሉት ሀገሮች አንዷ ስትሆን ከ3 ሺህ ዘመን በላይ ታሪክ አላት፡፡ ይህ 3ሺህ ዘመን የሚለው ታሪክ የሚጀምረው፤ ንግሥተ ሳባ በእሥራኤል ምድር ከክርስቶስ ልደት 900 ዓመት በፊት ነግሦ የነበረውን ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ሄዳ ቀዳማዊ ምኒልክን ከሱ ከወለደችበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡

ቀዳማዊ ምኒልክም ከአደገ በኋላ፤ አባቱ ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ሄዶ፤ ከእሥራኤል የበኩር ልጆች ጋር ሆኖ ጽላተ ሙሴ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ፤ የኦሪት እምነት በሀገራችን ተስፋፍቶ ነበር፡፡ እንደ አይሁድ ልማድም ወገኖቻችን በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ፤ የሚገባውን መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳኑ ላይ <<ጰራቅሊጦስ በቅድስቲቱ ከተማ በወረደ ቀን ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ>> በድርሳኑ ገልጿል፡፡

ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ ግን ኢትዮጵያውያን ከኦሪት እምነት ወደ ክርስትና ሲለወጡ እና፤ በ4ኛ ክፍለ ዘመን ክርስትና የሀገሪቱ ዋና እምነት ሲሆን፤ አባቶቻችን ወደ ቅድስት ሀገር በመሔድ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት ባደረገባቸው ቦታዎች ላይ አብያተ ክርስትያናትን በመመሥረት ለእኛ ታላቅ ቅርስ አቆይተዋል፡፡ የነገሥታቱም ዕርዳታ አልተለያቸውም ነበር፡፡


ይሁን እንጂ በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ፤ በወቅቱ ነግሠው የነበሩት አጤ ልብነ ድንግልም ሆኑ እሳቸውን የተኳቸው ነገሥታት፤ በጦርነቱ ምክኒያት በቅድስት ሀገር ለተቋቋሙ አብያተ ክርስትያናት ዕርዳታቸውን ስላቋረጡ፤ ካህናቱ የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ፣ ምግብ ባለማግኘታቸው፤ ገዳማቱን ግማሹን በአደራ ለአርመንና ለግሪኮች እየሰጡ፤ ሌሎቹን ደግሞ ዘግተው ወደ አውሮጳ ተሰደዱ፡፡ ከዓመታት በኋላ ተመልሰው ሲመጡ ግን ሁሉንም ለማግኘት ባይችሉም አሁን በእጃችን ያሉትን ይዘው አገልግሎታቸውን ቀጠሉ፡፡ ግራኝ ድል ሆኖ ጦርነቱ ከቆመም በኋላ፣ አንድ ወጥ መንግሥት የነበረው ቀርቶ የዘመነ መሳፍንት አገዛዝ ስለቀጠለና ፣ አሁንም በቂ ዕርዳታ ማግኘት ስላልቻሉ፤ ድርጎ፣ ልብስ፣ የመሳሰሉትን የሚያገኙት ከአርመንና ከግሪክ ገዳማት ነበር፡፡

በ19ኛ ክፍለ ዘመን የነገሡት ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ እና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ የወገኖቻችንን ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ ብለው ቋሚ ገቢ እንዲኖራቸው በማሰብ እዚያው ኢየሩሳሌም ውስጥ ሕንፃ

ተሠርቶ የሚከራይበት መሬትና ተጨማሪ ሌላ ባለ ሁለት ፎቅ ሕንፃ 1895 ዓ.ም. በመግዛት አበርክተዋል፡፡ በዚያው ዓመት የመድኃኔዓለምን ታቦት ዴር ሱልጣን መድኃኔዓለም በሚል ተሰይሞ መምህር ፈቃደ እግዚእ በተባሉ መነኩሴ ወደ ኢየሩሳለም ልከው በዴር ሡልጣን ገዳም ለ34 ዓመታት ሲቀደስበት ሲወደስበት ኖሯል፡፡



ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ ግንቦት 6 ቀን 1888 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን 200,000 ሺህ ማርትሬዛ ብር በባንክ እንዲቀመጥ አድርገው፤ በሚገኘው ወለድ በገዳሙ የሚኖሩት አባቶችና ለጉብኝት የሚሄዱት ወገኖቻችን እንዲጠቀሙ አደረጉ፡፡ ርዳታቸውም በዚህ አላበቃም፤ በዓመቱ ሌላ ሁለታ ሕንፃዎች አሠርተው ለገዳሙ አበርክተዋል፡፡ በተጨማሪም ሌላ 100,000 ማርትሬዛ ብር ለገዳሙ ዕድሳት ለግሰዋል፡፡ ዕርዳታቸውንም በመቀጠል ንዋየ ቅድሳት በመላክ፣ ደብዳቤ እየጻፉ በማበረታታት፤ ገዳማችንና ወገኖቻችን በክብር እንዲኖሩ አድርገዋል፡፡


የተላከ፡ከእቴጌ፡ጣይቱ፡ብርሃን፡ዘኢትዮጵያ ፡፡—
ይድረስ፡ ከማህበረ፡ዴር፡ሡልጣን፡ወደብረ፡ገነት፡ዘኢየሩሳሌ
ም፡ እጅግ፡እንዴት፡ናችሁ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ፡፡—
እስካሁንም፡ለለመላኪ፡ጠብቆ፡ድብልቅልቅ፡እያደረጋችሁ፡ባትሰማ
ሙ፡ነው፡፡—ለሁን፡ግን፡መሰማማታችሁን፡ለድኆታችሁን፡ከንሰማ፡እጅግ፡
ደስ፡አለን፡፡— እንግዲህ፡እንዲህ፡ስትሰማሙ፡ችሁልን፡ለንድኆታችሁ፡ካማረ፡
ፈናንጉን፡አባቶቻችንን፡ለትርሱን፡ለማለት፡እንተጋለን፡፡—ይናንተም፡እ
ዘኑ፡ሐዘናችሁ፡እንኳን፡ለኛ፡ለሊላም፡ሰው፡ተተርፋላችሁ፡፡—
እኔ፡ግራዝማች፡ነኝ፡እኔ፡ትግሬ፡ነኝ፡፡ እኔ፡ሸዋ፡ነኝ፡—እያሉ፡መጣላቱ፡ቀርቶ፡
፩ልብ፡ሁናችሁ፡ደጋታችሁን፡ድገሙ፡ወትው፡የሚጀምሩትን፡የንንዘብና፡
የታዳጊ፡እመት፡ነበር፡፡—እኛ፡ደህና፡ስሆን፡እንግዲህ፡ደህ፡ሁሉ፡ለይችግራች
ሁም፡፡ ታኅሣሥ ፴ ቀን፡ ፲፰፻፺፯ ዓመተ፡ ምሕረት፡ አዲስ፡ አበ
ባ፡ ከተማ፡ ተጻፈ፡፡

በ1886 ዓ.ም. በአድዋ ላይ በእምዬ ምኒልክ ድል ተደርጋ በዓለም ላይ መሳቂያ የሆነችው ኢጣሊያ፤ በ1928 ዓ.ም. ኃይሏን አጠናክራ ሽንፈቷን ለመበቀል ኢትዮጵያን ወረረች፡፡ ጀግኖች አባቶቻችንንም በተቻላቸው አቅም ቢዋጉም፤ በዘመናዊ መሣሪያ ታጥቆ የመጣውን የጠላትን ጦር መቋቋም አልቻሉም ነበር፡፡ የአድዋው ድል እንዳይደገምም የኢጣሊያን ጦር የተከለከሉ የመርዝ ጋዞች ከአውሮፕላን ላይ በመጣል ብዙዎች ወገኖቻችንን ጨረሱ፡፡ ይኽን አረመኔያዊ ሁኔታ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ለማመልከት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቅዳሜ ሚያዚያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም. ወደ ጅቡቲ በባቡር ተጓዙ፡፡ ከዚያም በእንግሊዝ የጦር መርከብ ሚያዚያ 26 ቀን ከጅቡቲ ተነስተው ሚያዚያ 30 ቀን ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ደረሱ፡፡



በኢየሩሳሌም በቆዩባቸው ጊዜያት በደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ሥርዐተ ቅዳሴውን በመሳተፍ፣ ስለ ሀገራችን በመጸለይ፣ ወገኖቻችንን በማበረታታት፣ ከሌሎች ታላላቅ ባለሥልጣኖቻቸው ጋር ምክክር እያደረጉ፣ የኢጣሊያ መንግሥት በሀገራቸውና በሕዝባቸው ላይ የሚያደርሰውን አሰቃቂ መከራና ግፍ በመዘርዘርና በመጻፍ፣ በጄኔቫ በሚገኙት የኢትዮጵያ መልእክተኞች አማካኝነት፤ የመንግሥታቱ ማኅበር እንዲያውቀው ደብዳቤ ይጽፉ ነበር፡፡

በሰኔ ወር 1928 ዓ.ም. ዐጤ ኃ/ሥላሴ በእንግሊዝ የጦር መርከብ ተሳፍረው ከኢየሩሳሌም ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄዱ፡፡ Southhampton ወደብ ሲደርሱ የእንግሊዝ ሕዝብ ደማቅ አቀባበል አደረገላቸው፡፡ ከ Southhampton ወደ ወናው ከተማ ለንደን በባቡር ተጉዘው Waterloo station ሲደርሱ፤ አሁንም የለንደን ሕዝብ ከፍ ያለ አቀባበል አደረገላቸው፡፡


ለንደን ከተማም ጥቂት ቀናት ከሰነበቱ በኋላ፤ ስዊዘርላድ ውስጥ ጄኔቫ በሚገኘው፣ የመንግሥታቱ ማኅበር ስብሰባ ላይ ለመገኘት ከአማካሪዎቻቸው ጋር ተጉዘው ጄነቫ በ Carleton Park Hotel አረፉ፡፡ ሰኔ 23 ቀን 1928 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ንጉሥ ነገሥቱ ለተሰበሰበው የመንግሥታቱ ማኅበር ንግግር ለማድረግ ወደ መድረኩ ላይ ሲወጡ፤ የጣሊያን ደጋፊዎች በፉጨትና በጩኸት ረብሸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ፀጥታ ከሰፈነ በኋላ ንግግራቸውን በመቀጠል የኢጣሊያ መንግሥት በሀገራቸውና ሕዝባቸው ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍ በመዘርዘር አስረድተው፤ እስካሁን ድረስ ሀገራቸው ላቀረበችው አቤቱታ የመንግሥታቱ ማኅበር ምንም ዓይነት አቋምና እርምጃ አለመውሰዱ እንዳሳዘናቸው ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም

እግዚአብሔርና ታሪክ ፍርዳችሁን ሲያስታውሱት ይኖራሉ በማለት ልብን የሚነካ ታሪካዊና ትንቢታዊ ንግግር አድርገው ወደ ኢንግላንድ ተመልሰው በባዝ ከተማ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የስደት ኑሮአቸውን ቀጠሉ፡፡

እሳቸውም ቃል ኪዳናቸውን አክብረው ይደርሱልኛል ብለው የተማመኑበት የመንግሥታቱ ማኅበር እንደጠበቁት ስላረዳቸው፤ በማኅበሩ ላይ ተስፋ በመቁረጥ፤ ፊታቸውን ወደ አባቶቻቸው አምላክ በማዞር በጾምና በፀሎት ለመማፀን በማሰብ፤ ቀደም ሲል በአፄ ምኒሊክ ወደ ኢየሩሳሌም ዴር ሱልጣን ገዳም ተልኮ አገልግሎት እየሰጠ የነበረው የመድኃኔዓለም ታቦት ከኢየሩሳለም ወደ እንግሊዝ እንዲላክላቸው፤ በጥር ወር 1929 ዓ.ም. አባ ሃና ጂማን ከእንግሊዝ ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ላኳቸው፡፡


በዚሁ መሠረት አባ ሃና ጂማ ታቦቱን ይዘው ከሌሎች 4 መነኮሳት (ስማቸው መምህር ገ/ኢየሱስ፣ አባ ማርቆስ፣ አባ ኃይሌ ቡሩክ እና አባ ገ/ማርያም) ጋር ወደ እንግሊዝ ተመለሱ፡፡ ጽላቱም ሚያዚያ 27 ቀን 1929 ዓ.ም. ባዝ ከተማ ደርሶ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ፡፡ ነፃነት ተመልሶ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ እስኪመለስ ድረስ ካህናቱ የፀሎትና የቁርባን ሥርዓት በመፈፀም፣ ስደተኞቹን በማስተማርና በማጽናናት የሚጠበቅባቸውን መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጡ ቆዩ፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ኢጣልያ ከጀርመን ጎን ስትሰለፍ፤ እንግሊዝ ዐጤ ኃ/ሥላሴን ለመርዳት ወሰነች፡፡ በዚህም መሠረት ሰኔ 17 ቀን 1932 ዓ.ም. ንጉሡን ወደ ግብጽ ከዚያም ወደ ሱዳን በመውሰድ፤ ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ለሚደረገው የጦር ዘመቻ ዝግጅት እንዲጀመር አደረገች፡፡ በሱዳን የነበሩ ብዙ ስደተኛ ኢትዮጵያን እንዲሁም ሌሎች ከኢትዮጵያ በመምጣት በካርቱም አስፈላጊውን የጦር፣ ልምምድና ዝግጅት ከተደረገ በኋላ፤ ከእንግሊዞች ጋር በመሆን ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ጦርነቱ ተጀመረ፡፡ ዐጤ ኃ/ሥላሴ ሱዳን ከደረሱ ከ7 ወራት በኋላ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም. ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በመግባት አሜድላ ላይ የኢትዮጵያ ባንድራ ሰቀሉ፡፡



ከዚያም በጎጃም ደብረ ማርቆስ አድርገው ወደ መሐል ሀገር እየገፉ በመሔድ ከሀገር በወጡ በ5 ዓመታቸው ሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም. በድል አድራጊነት ወደ መናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ በመግባት በቤተ መንግሥታቸው ባንዲራችንን ሰቀሉ፡፡

ቀጥሎም በስደት የነበረው ታቦት መድኃኔዓለም ነሐሴ 23 ቀን 1933 ዓ.ም. እቴጌ መነን ወደ አዲስ አበባ በተመለሱ ቀን፤ አባ ኃይሌ ቡሩክ ታቦቱን ይዘው ተመልሰው በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት የአሁኑ የስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ጸሎት ቤት ውስጥ እያጠኑና እየጠበቁ ከቆዩ በኋላ፤ ሚያዚያ 27 ቀን 1935 ዓ.ም. የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ተብሎ ተሰይሞ በቀድሞ ቤተ ሳይዳ ቀዳማዊ ኃ/ሥለሴ ሆስፒታል አሁን የካቲት 12 ቀን ተብሎ በሚጠራው ግቢ ውስጥ ተተከለ፡፡ የስሙም ትርጓሜ ለተበደሉትና ላዘኑት ማረጋጊያ ማጽናኛ ማለት ነው፡፡



ከአምስት ዓመት በኋላ ግ/ቀ/ኃ/ሥላሴ ቤተ ክርስቲያኑ አሁን በሚገኝበት ቦታ ላይ እንዲሠራ ሚያዚያ 27 ቀን 1940 ዓ.ም. የመሠረተ ድንጋይ አኖሩ፡፡ ሕንፃውም ከ2 ዓመት በኋላ ሚያዚያ 27 ቀን 1942 ዓ.ም. ተሠርቶ ተጠናቀቀ፡፡ በዋዜማው ሚያዚያ 26 ቀን ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኑ ቡራኬ ሥነ ሥርዓትና የሰዓታት ጸሎት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ሲካሄድ አደረ፡፡ ታቦቱም ከቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ግቢ ወጥቶ አዲስ ወደተሠራው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ገባ፡፡

ንጋት ላይ ልክ 12 ሰዓት ተኩል ላይ አጤ ኃ/ሥላሴና ንጉሣውያን ቤተሰቦች እንደደረሱ እና ብዙ ምዕመናን በተሰበሰቡበት የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት ተጀመረ፡፡ በዕለቱም የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት የተመራው በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ፣ አቡነ ቴዎፍሎስና፣ አቡነ ጢሞቴዎስ ነበር፡፡ ከቅዳሴውም በኋላ የገዳሙ አስተዳዳሪ የነበሩት አባ ሃና የታቦቱን የስደትና የመመለስ ታሪክ የሚገልጽ፤ ስብከት ለ15 ደቂቃ ካሰሙ በኋላ በስደት ሀገር ሲዘመር የነበረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር ተዘመረ፡፡ በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የቡራኬ ጸሎት አድርገው ናዝዘው፣ ሠርሆተ ሕዝብ ካደረጉ በኋላ፣ ታቦቱ ወጥቶ ሥርዓተ ዑደት ተደርጎ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል፡፡



ቤተ ክርስቲያኑ ተመርቆ አገልግሎት ከጀመረ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተስለው የሚታዩት ውብ ስዕሎች ሥራ በውጭ ሀገር ሰዓሊ የተሳሉት ከ1950 ዓ.ም  እስከ 1954 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ነው፡፡ እነዚህ ስዕሎች በአሁኑ ወቅት ቀለማቸው ለቆ ተጎድተው ይታያሉ፡፡ ገዳሙም እነዚህ ስዕሎች እንዲታደሱ የገንዘብ ማሰባሰብ ጀምሮ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሀገር ውስጥ አንደ መጀመሪያው አድርጎ ሊሠራቸው የሚችል ሰዓሊ ስላልተገኘ፤ የውጭ ሀገር ሰዓሊዎች እንዲሠሩ ሞክሯል፡፡ ይሁን እንጂ ወጪው በጣም ብዙ ስለሆነ ለጊዜው ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ ተደርጓል፡፡

ይህ ገዳም ራሱን እንዲችል ለማድረግ አባ ሃና በገንዘብና ከግል ርስታቸው 1 ጋሻ መሬት በመስጠት እንዲረዳበት ሰጥተዋል፡ ፡ ንጉሣውያን ቤተሰቦችም አክሲዬን በመግዛት ይህን ገዳም ረድተዋል፡፡ ገዳሙ ራሱ የካህናት ኑሮ እንዲሻሻል ለማድረግ የሥጋጃ ሥራ በመክፈል ጥረት አድርጓል፡፡

የምስካየ ኅዙናን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ከቀን ወደ ቀን እየተሻሻለ እያደገ የመጣ ሲሆን፤ ገና ከመሠረቱ አንስቶ ልዩ የሚያደርገው አገልግሎቱ በአብዛኛው በአማርኛ ቋንቋ መከናወኑ ነው፡፡ እንዲሁም የማታ ስብከት መርሐ ግብር በማዘጋጀት ከሁሉም ቀዳሚ ነው ቢባል ማጋነን  አይሆንም፡፡ በሰሙነ ሕማማት የሚካሄደው አጠቃላይ መርሐ ግብር በብዙዎች ላይ ትዝታን የሚያመጣ ነው፡፡

ይህ ገዳም ከቀልጣፋ መንፈሳዊ አገልግሎት ባሻገር በሥሩ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ክፍሎች አሉት፡፡ ከእነዚህም አንዱ <<የተምሮ ማስተማር ማኅበር>> በሚል ስያሜ የሚታወቀው የሰንበት ት/ቤት ነው፡፡ የተምሮ ማስተማር ማኅበር መሥራች አባላት መጀመሪያ እንቅስቃሴያቸውን የጀመሩት፡ ቤተ ክርስቲያኑ አሁን ካለበት ቦታ ከመመሥረቱ በፊት፤ በአሁኑ የእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም በቀድሞ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ይማሩ የነበሩ ወጣቶች ስለ ሃይማኖታቸው ለመጠየቅና ለማጥናት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን ለመከታተል የተጣሉ ጓደኞቻቸውን ለመምከርና ለማስታረቅ በየእሑድ የሚሰበሰቡበትን መርሐ ግብር በ1939 ዓ.ም. ጥቂት ሆነው  እት/ቤት ውስጥ ባለ ዛፍ ጥላ ሥር ጀመሩ፡፡

ይህ በጥቂት ወጣቶች የተጀመረ እንቅስቃሴ፤ ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው እየጨመረ ሲመጣ፤ ከአጠጋባቸው ወደ ተተከለው ወደ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በመምጦት ከሥርዓተ ቅዳሴው በኋላ በ4፡00 ሰዓት በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቅርብ በሚመጡ መንፈሳዊ መምህራን አማካኝነት፤ ትምህርት በቋሚነትና በስፋት ይሰጣቸው ጀመረ ወዲያውም በቀድሞ የእቴጌ መነን ት/ቤት ወይም በአሁኑ የካቲት 12 አጠቃላይ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ ወጣት ሴቶች በየእሑዱ መርሐ ግብር መሳተፍ ጀመሩ፡፡

የዕለተ እሁድ መርሐ ግብር እያደር እያደገ በመሔዱ በመጨረሻ በወጣቶቹና በቤተ ክርስቲያኑ አገልግጋዬች መካከል ስምምነት ተደርሶ በ1955 ዓ.ም. “የተምሮ ማስተማር ማኅበር” በሚል ስም ተሰይሞ ከተለያዩ ምዕመናንና ከቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ተሰባስቦ፤ ለማኅበሩ መገልገያ የሚሆን ጽ/ቤትና አዳራሽ በ26 ሺህ ብር ተሠርቶ እስከ ዛሬ ድረስ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ከዚያ ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያነፀ በማውጣት ላይ ይገኛል፡፡



የተምሮ ማስተማር ማኅበር ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ከመደበኛው መርሐ ግብር በተጨማሪ አዳዲስ አቀራረቦችና ዘዴዎችን ለመንፈሳዊ አገልግሎትና ትምህርት አሰጣጥ በማመንጨት እየተጠቀመ ይገኛል፡፡ ከነዚህም በጥቂቱ፡-

- በተለያየ ጊዜያት ወደ ማኅበሩ የሚመጡ አዲስ አባላትን ተቀብሎ ለአንድ ዓመት የሚሰጥ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ኮርስ እየሰጠ በየዓመቱ ከ300-400 የሚደርሱ ወጣቶችን ያስመርቃል፡፡
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለምሳሌ የ6 ኪሎ፤ 5 ኪሎ፣ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ዘወትር እሁድ ከቅዳሴ በኋላ በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ መንፈሳዊ ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
- መስማት ለተሣናቸው ወጣቶች እንደሌሎቹ ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲታነጽ መርሐ ግብር በማዘጋጀት እንዲማሩ ያደርጋል፡፡
- በየዓመቱ በሆሣዕና በዓል ዕለት የበዓሉን መታሰቢያነት በማመልከት የአህያ ውርጭንላ ይዞ የበዓሉን መዝሙር እየዘመሩ፤ ስድስት ኪሎ አደባባይ ድረስ ሄዶ በመመለስ ያከብራሉ፡፡

ይህ ማኅበር በዕለተ ሰንበትና በዕየለቱ ማታ የሰብከት ጊዜ መንፈሳዊ ዜማዎችን እንዲሁም በሰሙነ ሕማማት ሳምንት የቆዩ መዝሙራትን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በማሰማት የመዝሙር አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ ሲሆን በመዝሙርም ሆነ በስብከተ ወንጌል አገልግሎት በመላው ኢትዮጵያ ሰንበት ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገና ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ነው፡፡ እንዲሁም ቀደም ባለው ጉዜ ታቦታት በጀን ሜዳ ወጥተው በሚከበርበት ወቅት፤ መንፈሳዊ ትምህርትንና የመዝሙር አገልግሎትን በመስጠት ቀደምትነት ያለው መንፈሳዊ ማኅበር ነው፡፡

ለዚህ ለማኀበር ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጾ ካደረጉት ዋናው አንዱ አቶ አበበ ከበደ ነበሩ፡፡ የደርግ መንግሥት እኝህን ሰው በእስር ቤት አለ አግባብ አሥሮ በሚያንገላታቸው ወቅት፣ እሳቸው ግን ከእስር ቤት ደብዳቤ እየጻፉ “ ማኅበራችን እንዴት ነው? በርቱ” እያሉ የሚከታተሉ ነበር፡፡ እኝህ ታላቅ ሰው በአረመኔው ደርግ በ1967 ዓ.ም. በግፍ ተገድለዋል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ነፍሳቸውን ይማር፡፡

ሁለተኛውና በዚህ ገዳም ሥር የሚገኘው ሌላው ተቋም የምስካየ ኅዙናን ገዳም ት/ቤት ነው፡፡ ይህ ት/ቤት የሕንፃ ግንባታው የተጠናቀቀው በ1965 ዓ.ም ሲሆን የ1ኛ ደረጃ ትምህርት  መስጠት የጀመረው በ1966 ዓ.ም. በ40 ሕፃናት እና በሁለት መምህራን ነበር፡፡ ትምህርት ቤቱ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ በየዓመቱ በሚሰጠው የ6ኛ እና 8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተማሪዎቹ ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገባቸው ታዋቂነቱ እየጨመረ ሄዶ፡፡




ት/ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በየዓመቱ አንድ ክፍል የደረጃ ዕድገት በመጨመር 1988 ዓ.ም. ጀምሮ የተሟላ 2ኛ ደረጃ ለመሆን በቃ፡፡ በ1991 ዓ.ም. ት/ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ተማሪዎች እንዲወስዱ አድርጓል፡፡ ይህ ዘመናዊ ት/ቤት ለሕፃናትና ወጣቶች  ከሚሰጠው ከፍ ያለ የመንፈስ ብልጽግና በላይ፤ በእነሱ አማካኝነት በምዕመናንና በቤተክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት የበለጠ እንዲጠናከር አድርጎታል፡፡




ገዳሙ የገቢ ምንጩን ለማዳበር፣ እንዲሁም የአካባቢው ማኅበረሰብ ይጠቀምበት ዘንድ፤ አነስተኛ ክሊኒክ ከፍቶ ብዙዎች በተመጣጣኝ ዋጋ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል፡፡




ከዚህ ክሊኒክ ሌላ የሻይ ቤት በመክፈት ገቢውን ከማዳበሩ ሌላ፤ በአካባቢው ላሉ ወጣቶች የሥራ ዕድልን ፈጥሯል፡፡ እንዲሁም በቅርቡ ገዳሙ ከቤተ ክርስቲያኑ ተሻግሮ ባለው ቦታ ላይ ባለ 6 ፎቅ ሕንፃ ሠርቶ ለባንክና ለተለያዩ ድርጅቶች በማከራየት ይጠቀማል፡፡



የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም  ዐጤ ምኒልክ ታቦቱን ወደ ቅድስት ሀገር ልከው፤ ከዚያም በእንግሊዝ ሀገር በስደት ለብዙዎች መጽናኛ ሆኖ ቆይቶ ወደ ሀገራችን ተመልሶ እስከመጣበትና እስከ አሁንም ድረስ፤ ታሪካዊና፣ በሥራ ሂደቱ፣ በእንቅስቃሴው፣ ልዩ ልዩ ሥራዎችን በመጀመር ለሌሎች አብያተ ክርስቱያናት አርአያ በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ገዳም ነው፡፡

ወደፊትም የበለጠ ሥራ የሚሠራና፤ ለእናት ቤተ ክርስቲያናችን የሚያኮራ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ቸሩ መድኃኔዓለም ይህንን እና ሌሎቹን ገዳሞቻችንን እንዲጠብቅልን፤ ሀገራችንንም በበረከቱ እና ቸርነቱ እንዲጎበኝልን ዘወትር እንጸልያለን፡፡

አስጀምሮ ላስፈጸመን አምላክ ምስጋና ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን፡፡

በእደ ማርያም እጅጉ

ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ.ም